የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# የ2014 በጀት ዓመት የተስተካከለ ዕቅድ

ሕዳር 2014ዓ/ም

አዲስ አበባ

# Table of Contents


ክፍልአንድ ....2

1. መግቢያ ....2

1.1 የዕቅዱ ዋናዓላማ ....2

1.1.1 ዝርዝር ዓላማዎች ....3

ክፍልሁለት....3

2. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ ....3

2.1. የቋሚ ኮሚቴው የ2013 በጀት ዓመት ቁልፍ ችግር፡-....3

2.2. የቋሚ ኮሚቴው ቁልፍ ተግባር፡-....3

2.3 የቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ጥንካሬዎችና ውስንነቶች ....3

2.4.የውጫዊና የውስጣዊ ሁኔታዎች ግምገማ መነሻዎች....4

2.4.1. የውጫዊ ሁኔታዎች....4

2.4.2. የውስጣዊ ሁኔታ ግምገማ....6

ክፍል ሦስት....6

3. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ....6

3.1. ቁልፍ ተግባር....6

3.1.1 ዋና ተግባር....7

3.1.2 ዝርዝር ተግባራት ....7

4.የዓበይት ተግባራት ዕቅድ ግቦች....7

5. በዝግጅት ምዕራፍ የሚፈፀሙ ተግባራት ....8

6. በተግባር ምዕራፍ የሚፈፀሙ የዓበይት ተግባር ግብ፣ዋናና ዝርዝር ተግባራት ....10

7. የማጠቃለያ ምዕራፍ....17

8.የአፈፃፀም አቅጣጫዎች ....18

9. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት....19

10. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ ሐሳቦች....20

10.1 ችግሮች ....20

10.2 የመፍትሔ ሀሳቦች ....20

11.ማጠቃለያ ....21

# ክፍልአንድ

## 1. መግቢያ

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገመንግስት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ከሕዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት የሚያስችል በግልፀኝነት፣ በተጠያቂነት እና በአሳታፊነት ላይ የተመሰረተ የአደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ሕዝባዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡ እንዲሁም  አገራዊ  ርእይን ታሳቢ ያደረገ ዕቅድ ከተቋማዊ ተልእኮ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ጋር በማጣጣም እና ምክር ቤቱም የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/19/ እና አንቀጽ 59/2/ መሠረት እና የምክር ቤቱን  የቋሚ ኮሚቴ አሠራርና አደረጃጀት ውሣኔ ቁጥር 3/2014 በማውጣት ልዩ ልዩ ተግባራት ያላቸውን 11 /አሥራ አንድ/ ኮሚቴምችን አቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ምክር ቤቱ ካቋቋማቸው 11 /አሥራ አንድ/ የቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ አንዱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴው የአሰራርና አደረጃጀት ውሣኔ ቁጥር 3/2014 ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ታሳቢ በማድረግ የ2014 በጀት ዓመት የምክር ቤቱን መሪ ዕቅድ፣ የ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎችና እጥረቶች በመገምገም እንዲሁም የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርትና የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደመነሻ በመውሰድ፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋለውን የፀጥታ ችግሮችን ጨምሮ ተገማች መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶችን ታሳቢ በማድረግ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

### 1.2 የዕቅዱ ዋናዓላማ

አሁን በሥራ ላይ ያለው ምክር ቤት 6ኛውን ዙር ብሔራዊ ምርጫ ተከትሎ የተመሰረተ አዲስ ምክር ቤት እንደመሆኑ መጠን፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የፀጥታ ችግሮች ቢኖሩም፤ በኢትዮጵያ የተጀመረውን ለውጥ ለማስቀጠል ቋሚ ኮሚቴው የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚከታተላቸው መስሪያ ቤቶች ላይ የተጠናከረ የክትትል፣ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራን በማከናወን፣ የሚቀርቡ ረቂቅ ሕጎች በዝርዝር በማየት ሕግ ሆነው እንዲፀድቁ በማድረግ መስሪያቤቶቹ የተጣለባቸውን የሕዝብንና አገርን ተጠቃሚ

የሚያደርግና የመንግሥትን ሀብት ከብክነትና ከሌብነት በፀዳ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡

### 1.2.1 ዝርዝር ዓላማዎች

- የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልቶችን በመጠቀም የኮሚቴውን አመራርና አባላት አቅም በመገንባት የሌብነት አመለካከትና ተግባርን በመታገል እና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ጠንካራ የክትትል፣የቁጥጥርና የድጋፍ ሥራ በመሰራት ተልእኮቻቸውን እንዲወጡ ማስቻል፤
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተለውን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ከዕቅድ ዝግጅት እስከ ዕቅድ አፈፃፀሙ ድረስ በመደገፍ እና በመከታተል የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች በምክር ቤቱ የፀደቀ በጀትና አጠቃላይ ሀብት በተቀመጠለት አሰራር ሕግን፣ ደንብንና መመሪያን መሰረት በማድረግ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት እንዲያደርግ መከታተልና አፈፃፀሙን በሕዝብ ይፋ ውይይትና በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ፤

# ክፍልሁለት

## 2. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ

### 2.1. የቋሚ ኮሚቴው የ2013 በጀት ዓመት ቁልፍ ችግር፡-

- *ተጠያቂነት አለማረጋገጥ፡፡*

### 2.2. የቋሚ ኮሚቴው ቁልፍ ተግባር፡-

- ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡፡

### 2.3 የቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ጥንካሬዎችና ውስንነቶች

<u>ጥንካሬዎች</u>

- የታቀዱ ተግባራት በዕቅዱ መሠረት መተግበራቸው፣
- የአቅም ግንባታ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸው፣
- ሁሉም የቋሚ ኮሚቴ አባላት በንዑሳን ኮሚቴም ይሁን በቋሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ጊዜ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ካልሆነ በስተቀር የማይቀሩ መሆኑ፤

- ሥራዎችን የጋራ በማድረግ በቡድን ስሜት ለመንቀሳቀስና ተግባራትን ለማሳካት የሚደረግ ጥረት ጥሩ መሆኑ፣
- ከምክር ቤቱ የተመሩ አንድ አዋጅና አንድ ደንብ እንዲፀድቁ መደረጉ፣

<u>ውስንነቶች</u>

- ሚዲያዎች ለኦዲት ግኝቱና ለይፋዊ የሕዝብ ውይይቱ በበቂ ሁኔታ ትኩረት አለመስጠታቸው፣
- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት በተደጋጋሚ በይፋዊ ውይይት ጊዜ በቂ የሚዲያ ባለሙያዎችን አለመመደቡ፣
- አብዛኞቹ ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በኦዲት ግኝት መሰረት የድርጊት መርኃ-ግብር አዘጋጅተው ለዋና ኦዲተር አለመላካቸው እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ መውሰዳቸውን አለማሳወቃቸው፣
- አብዛኞቹ መስሪያ ቤቶች የመንግስት ሀብትና ንብረትን በአግባቡ አለመያዛቸውና የኦዲት ግኝትን ማስተማሪያ አድርገው አለመውሰዳቸው፣
- አብዛኞቹ መስሪያ ቤቶች የመንግስት የሒሳብ አያያዝ መመሪያን አክብረው ካለመስራታቸው ባሻገር የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ለኦዲት ግኝቶች ትኩረት ስላልሰጡ ለኦዲት ግኝቶች ተገቢ ማስተካከያ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የባለድርሻ አካላት ተወካዮች በተሟላ መልኩ በይፋዊ መድረኮች አለመሳተፍና ወጣ-ገባዎች መታታቸው፣

## 2.4.የውጫዊና የውስጣዊ ሁኔታዎች ግምገማ መነሻዎች

### 2.4.1. የውጫዊ ሁኔታዎች

#### *2.4.1.1. መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች*

ሀ. መልካም አጋጣሚዎች

- መንግሥት ለምክር ቤቱ መጠናከር ቁርጠኛ አቋም መያዙ በተሻለ ሁኔታ በተነሳሽነት ለመስራት ምቹ አጋጣሚ መሆኑ፣
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፕሬዚዳንት ለሕዝብ ተወካዮት ምክር ቤት ያቀረቡት የ5 ዓመት የመንግሥት አቅጣጫ ንግግር ላይ ሌብነትን የሚጠየፍና የሥራ ታታሪነትን

የሚወድ ትውልድ መፍጠር ቁልፍ የመንግስት አቅጣጫ መሆኑን ማመላከታቸው፣

- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በበዓለ ሲመታቸው መንግስታቸው ሌብነትን ለመዋጋት ቁርጠኛ መሆኑን አንክሮ ሰጥተው አቅጣጫ በማስቀመጣቸው የተፈጠረው አገራዊ መነቃቃት እንዲሁም ኅብረተሰቡ በምክር ቤቱ ያሳደረው አመኔታና ተስፋ፣
- የኅብረተሰቡ የሞጋችነት፣ የተጠቃሚነት እና የሚዲያ ፈላጊነት ባሕል እየዳበረ መምጣት፣
- በ2013 የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያጋጠሙትን ችግሮች ለመፍታት አስቻይ የአዋጅ ማሻሻያና ደንብ መጽደቃቸው፣

**ለ. ስጋቶች**

- የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ለሕዝብ ይፋ ውይይቱ ተዘጋጅተውና ትኩረት ሰጥተው አለመምጣት፣
- ባለ ድርሻ አካላት ባወጡት ዕቅድ መሠረት ተገቢውን ክትትልና የደረሱበትን ሪፖርት አለማድረግ፣
- በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮች ቋሚ ኮሚቴው በሚያከናውናቸው የመስክ ምልከታ ስምሪቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ይችላል፡፡
- በዓለም የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚቀጥል ከሆነ የቋሚ ኮሚቴውን ዕቅድ በተለይም ይፋዊ የሕዝብ አስተያየት ማዳመጥ ዕቅዶችን ለመፈፀም አስቸጋሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች ያጋጠሙ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት የተያዙ ዕቅዶችን በአግባቡ ለመተግበር የበጀት እጥረት ሊያጋጥም ይችላል፡፡
- ባጋጠሙ አገራዊ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት የሚፈጠሩ ሕገ ወጥነቶች የቋሚ ኮሚቴውን ዕቅዶች ለመፈፀም አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

**2.4.2. የውስጣዊ ሁኔታ ግምገማ**

*2.4.2.1. ጥንካሬዎችና ውስንነቶች*

ሀ. ጥንካሬዎች

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና የሙያ ስብጥር ብዝኃነት፣
- የቋሚ ኮሚቴ አባላት ለሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኛ መሆናቸው፣
- ቋሚ ኮሚቴው የሥራ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መደገፉ፣

ለ. ውስንነት

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት ለኮሚቴው ሥራ አዲስ መሆናቸው፣

# ክፍል ሦስት

## 2. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

**<u>እሴቶች</u>**

- በዕቅድ መመራት
- የሕግ የበላይነትን ማክበር
- መቻቻል፣ መግባባትና መማማር
- ኃላፊነትና ተጠያቂነትን እውን ማድረግ

**3.1. ቁልፍ ተግባር**

- በዋና ኦዲተር ኦዲት ግኝት መነሻ በማድረግ የክትትል፣ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን፤

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የኮሚቴው አባላት በምክር ቤቱም ሆነ በሌሎች አካላት በሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ ግምገማዎችና ስብሰባዎች በመሳተፍ፣ የኦዲት ሰነዶችን በመመርመርና ከዕለት ተዕለት ተግባራት የማስፈፀም አቅማቸው መገንባት።

**3.1.1 ዋና ተግባር**

- በምክር ቤቱና በተለያዩ አካላት በሚመቻቹ ሥልጠናዎች፣ አውደጥናቶች እና እርስ በእርስ በመማማር የአባላት አቅም እንዲገነባ ማድረግ፣

**3.1.2 ዝርዝር ተግባራት**

- የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድና ሪፖርቶች በዝርዝር በማዘጋጀት በማንበብና በዕቅድ ኦሬንቴሽን እንደአቅም መገንቢያ መጠቀም፣
- የኦዲት ግኝት የተገኘባቸው አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችን የግኝት ሪፖሪት በማንበብ እንደአቅም መገንቢያ መጠቀም፣
- በምክር ቤት ጽ/ቤት፣ በቋሚ ኮሚቴዎች እና በተለያዩ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች በሚመቻቹ ሥልጠናዎች ላይ አባላትን በማሳተፍ የሚገኙ እውቀቶችንና ልምዶችን መጠቀም፤
- አባላት የተለያዩ የኦዲት ሪፖርቶችን በመመርመር ለሕዝብ ይፋዊ ውይይት መድረኮች ዝርዝር እና ቼክሊስቶችን/ጥያቄዎችን እንዲያዘጋጁና በመስክ ጉብኝት እንዲሳተፉ እና ከዕለት ተዕለት ተግባራት አቅማቸውን እንዲገነቡ ማድረግ፣
- ከሁሉም ይፋዊ የሕዝብ ውይይት መድረኮች እና ከመስክ ምልክታ በኋላ አፈፃፀሙን በጥልቀት በመገምገም እንዲሁም ዝርዝር ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና የተገኙ ልምዶችን የጋራ በማድረግ የአባላትን አቅም መገንባት፣
- በአገር ውስጥና የውጭ አገራት ሥልጠናዎችና መድረኮች የሚሳተፉ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ላልተሳተፉ አባላት ያገኙትን ግንዛቤ እና ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ፣
- ስለቋሚ ኮሚቴው ተልዕኮዎችና የእውቀት፣የክኂልና የአመለካከት ብቃት እንዲጠናከር በኮሚቴ ውስጥ ውይይት ማድረግ፣
- ከምክር ቤቱና ከተለያዩ አካላት ለኮሚቴ አባላት ከሚሰጡ የስብሰባና የሥልጠና ዕድሎች በተጨማሪ የኮሚቴውን ተልዕኮ ለማሳካትና ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ባላቸውን ሁለት /2/ የሥልጠና ርእሶች ላይ በቋሚ ኮሚቴው ደረጃ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠናዎች/የተሞክሮ ልውውጥ ጉብኝቶች ማዘጋጀት፡፡

# 4.የዓበይት ተግባራት ዕቅድ ግቦች

ግብ1.

- የተከናወኑ ጠንካራና ብቃት ያለዉ የክትትል ቁጥጥር ስራዎች

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች በምክር ቤቱ የፀደቀ በጀትና አጠቃላይ ሀብት በተቀመጠለት አሰራር ሥርዓት መሰረት ሕግ፣ ደንብና መመሪያን መሠረት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የተደረጉ ጠንካራ የክትትል፣የቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎች፡፡

<u>ግብ2</u>.

- የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ መሰረት የተረጋገጠ ተጠያቂነት

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ መሰረት ተጠያቂነት ይረጋገጣል ፡፡

<u>ግብ3.</u>

- የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አፈፃፀም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የተደረገ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ፡፡

  <u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አፈፃፀም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

## 5. በዝግጅት ምዕራፍ የሚፈፀሙ ተግባራት

ዋና ተግባር 1

- የቋሚ ኮሚቴው 2014 ዕቅድና የሥራ መከታተያ ቼክሊስት በማዘጋጀት ከዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትና ከኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የጋራ ማድረግ፡፡

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- ዋና ኦዲተር የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የኦዲት ግኝት ሪፖርትን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል የኮሚቴው ዕቅድና ቼክሊስት በማዘጋጀት ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ መስራት፡፡

ዝርዝር ተግባራት

- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድና ቼክሊስት በማዘጋጀት በአስተባባሪ ኮሚቴ ሲድቅ ሥራ ላይ ማዋል፡፡
- የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የዓመቱ የኦዲትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- የቋሚ ኮሚቴው የ2014 ዓ.ም የዝግጅት ምዕራፍ በጋራ በመገምገም ለቀጣይ ጊዜ ትምህርት መውሰድ፡፡

ዋና ተግባር 2

- የኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም የ2014 በጀት ዓመት የፎረሙ የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ሁሉም አባላት በተገኙበት ውይይት ተደርጎ እንዲፀድቅ ማድረግ፣ በቀጣይ አቅጣጫ ላይም በጋራ ውይይት ማድረግ፡፡

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የኦዲት ግኝት ሪፖርት ባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም በማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ትስስር በመፍጠር ሁሉም የፎረሙ አባላት የመንግስት ሀብትና ንብረት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማስቻል ሚናቸውን በጋራ እንዲወጡ ማስቻል፡፡

ዝርዝር ተግባራት

- የኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም የ2013 በጀት ዓመት የፎረሙ አፈፃፀም ግምገማ መነሻ በማድረግ የየራሳቸውን የ2014 ዕቅድ በማዘጋጀት ለቋሚ ኮሚቴ እንዲልኩ ማድረግ፡፡
- ተዘጋጀቶ የመጣውን ዕቅድ በኮሚቴ ደረጃ የሁሉንም በአንድ ላይ በማደራጀት አንድ ወጥ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡
- በተዘጋጀው የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትና ባለድርሻ አካላትን በመጥራት ውይይት በማድረግ ማስፀደቅ፡፡
- በዕቅዳቸው መሰረት ተግባራቸውን መፈፀም አለመፈጸማቸው የሚገመገምበት የጋራ ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ የጊዜ ገደብ አቅጣጫ ማስቀመጥ፡፡

## 6. በተግባር ምዕራፍ የሚፈፀሙ የዓበይት ተግባር ግብ፣ዋናና ዝርዝር ተግባራት

ግብ 1

- የተከናወኑ ጠንካራና ብቃት ያለው የክትትል፣ የቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎች፡፡

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች በምክር ቤቱ የፀደቀ በጀትና አጠቃላይ ሀብት በተቀመጠለት አሰራር ሥርዓት መሰረት ሕግን፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ በይፋ ሕዝብ ውይይትና በመስክ ሥራ ጠንካራና የክትትል፣የቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

ዋና ተግባር 1

- በፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የኦዲት ግኝት ሪፖርት መሰረት በኦዲት ተደራጊ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች እና የተገኙ ውጤቶች የዋና ኦዲተር መ/ቤት መስሪያ ቤት ተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ይፋ የሕዝብ ውይይት በማካሄድ የቁጥጥር፣የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን መፈፀም፡፡

ዝርዝርተግባራት

- በ2014 በጀት ዓመት <u>26</u> የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በምክር ቤቱ የፀደቀላቸውን በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ፣ ደንብ እና መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ለታለመለት ዓላማ ማዋላቸው በፋይናንስ ሕጋዊነትና በክዋኔ ኦዲት ግኝት መሰረት በማድረግ በይፋ የሕዝብ ውይይት መድረኮች ክትትልና ቁጥጥር የማረጋገጥ ሥራ መስራት እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር ዕቅድ እና ሪፖርት ክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን፡፡
- የኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የጐላ ችግር ያለባቸው በመሆናቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለሚከታተሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መረጃ መስጠትና ውጤቱን መከታተል፡፡

- የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የድጋፍና የኦዲት ዘርፍ የዓመቱን ዕቅዱ ገምግሞ ግብረ መልስ መስጠት፤ በተመሣሣይ በዕቅዱ መሰረት የሩብ፣ የግማሽ ዓመትና የዓመቱን ሪፖርት በወቅቱ ገምግሞ ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- የዋና ኦዲተር ዓመታዊ ሪፖርት ለቋሚ ኮሚቴው አስቀድሞ እንዲደርስ በማድረግ ገምግሞ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የተሟላ ሪፖርት ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ ማድረግ፡፡
- የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የሀብትና በጀት አጠቃቀም ወጪ ቆጣቢና ከብክነት ነፃ የሆነ አሠራር መኖሩን፣ ለሁሉም ፕሮግራሞች በጀት መመደቡን እና የሰው ሀብት ቅጥርና የደረጃ ዕድገት ሕግና መመሪያን ተከትሎ መፈፀሙን ማረጋገጥ፣ ለውስጥ ሠራተኞች የሚሰጡት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ክፍተትን ለመሙላት የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የሌብነት አመለካከት ተግባራትን ለመዋጋት፣ የሀብት ብክነትና የሚያጋልጡ አሰራሮችን ለይቶ ከምንጫቸው ለማድረቅ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በትኩረት መከታተል፡፡
- የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በዕቅድ ይዘው እየሰሩ መሆናቸውን በተለይም የሕዝብ ክንፍ ከመፍጠር አኳያ ያለውን ሁኔታ በደንብ መከታተል፣በዕቅድ ደረጃ የመሰረታዊ አሰራር ለውጥ (BPR) እና ሚዛናዊ ስኮር ካርድ (BSC) አተገባበር መሰረት አድርገው ማቀዳቸውን ማረጋገጥ፣ መገምገምና መደገፍ፤ እንዲሁም የሰውና የቁሳቁስ አደረጃጀታቸውና አሰራራቸውን በክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማረጋገጥ፡፡
- በ2014 በጀት ዓመት ኮሚቴያችን በ26 መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የሕዝብ ይፋ ውይይት መድረክ በማድረግ እና የገጠርና 6 የከተማ 6 መስክ ሥራዎችን በመሥራት የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በኦዲት ግኝት ሪፖርቱ መሰረት ማስተካከያና የእርምት እርምጃ እንዲወሰዱ ግብረ መልሶች መስጠት፤ በዚሁም መሰረት የተሰጣቸውን ግብረ መልስ ተቀብለው የተገበሩና ያልተገበሩትን በቁጥጥርና ክትትል ሂደት የመለየት ሥራ መስራት።

ዋና ተግባር 2

- ቋሚ ኮሚቴው የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች የተሰጣቸውን የማስተካከያ አስተያየት መነሻ ማሻሻያ ማድረግ አለማድረጋቸውን በገጠርና በከተማ መስክ በመገኘት የቁጥጥር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን እና በሚከታተለው ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ላይም በመስክ ክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሥራ መስራት፡፡

ዝርዝርተግባራት

- በ2014 በጀት ዓመት 6 የገጠርና 6 የከተማ መስክ በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ የመስክ ሥራዎች መስራት፡፡
- ለመስክ ምልከታው የሚያግዙ መረጃዎችን አስቀድሞ መሰብሰብ፡፡
- ለገጠርና ለከተማ መስክ ምልከታ ቼክሊስት ማዘጋጀት፡፡
- በመስክ ምልከታው የሚሳተፈውን የሰው ኃይል መለየት፡፡
- በመስክ ምልከታ ወቅት የፌዴራል መንግስት ተቋማትና ድርጅቶች መንግስት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሰረት መመራቱን በመገምገም በክትትልና ቁጥጥር ተግባር የማረጋገጥ ሥራ ማከናወን፡፡
- የመስክ ሪፖርቱን በወቅቱ በማዘጋጀት ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ፡፡
- በመስክ ምልከታው የተገኙ መልካም ተሞክሮች ካሉ በማደራጀት ሌሎች መስሪያ ቤቶችና ተቋማት እንዲጠቀሙበት ማድረግ፡፡
- የመስክ ምልከታ ሪፖርቱን በወቅቱ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ማድረግ፡፡
- በመስክ የተገኙ ግኝቶችን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በአካል መገምገም፡፡
- በአጠቃላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በአካል በመገኘት በኦዲት ግኝት ሪፖርቶች መሰረት መስሪያ ቤቶች በእርምጃ አወሳሰድ ያላቸውን ክትትልና ያጋጠማቸው ችግርም ካለ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚፈቱበትን አቅጣጫ ማስቀመጥ፡፡
- እንደየኦዲት ግኝቱ ሁኔታ በምክርቤቱ ካሉ ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር እና ከኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የቅንጅት ዕቅድ በማዘጋጀት በጋራ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ የመስክ ምልከታ ማድረግ።

ግብ2.

የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ መሰረት የተረጋገጠ ተጠያቂነት፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

የኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ መሰረት ተጠያቂነት ይረጋገጣል

ዋና ተግባር 3

- ቋሚ ኮሚቴው የኦዲት ግኝትን መሰረት በማድረግ የኦዲት ተደራጊ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር የውይይት መድረክ በመፍጠር ሥራዎችንም በጋራ ማከናወን፡፡

<u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

- የተደራጀና የተቀናጀ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት በምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው የተሰጡ ተልዕኮዎችን በተሟላና በተቀናጀ ሁኔታ በመተግበር የሕዝብና የመንግስት ሀብትና ንብረት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማስቻል፡፡

ዝርዝር ተግባር

- ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በቅንጅትና በተናጠል የሚሰሩ ተግባራትን በመለየት የጋራ ዕቅድ በማውጣት መፈፀም፡፡
- በተፈጠረው ቅንጅቶች አማካኝነት በየሩብ ዓመቱ ሥራዎችን መገምገም ጥንካሬና እጥረቱን በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡
- በይፋ መድረኮች ላይ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ተገኝተው ሀሳብ እንዲሰጡ ማስቻል፡፡
- ከአፈ ጉባዔዎች የጋራ መድረክ የሚገኙ ተሞክሮዎችን በመቅሰም ለክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማዋል፡፡
- ከሌሎች በምክር ቤቱ ከሚገኙ ቋሚ ኮሚቴዎች መልካም ልምድ መቅሰም፡፡

ዋና ተግባር 4

- የሕዝብ ክንፍ አካላት በኦዲት ግኝት ሪፖርት ይፋ የሕዝብ ውይይት መድረኮች ላይ በበቂ ሁኔታ እና በባለቤትነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚያስችል የቁጥጥርና ክትትል ተግባራት ማከናወን፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

- የሕዝብ ክንፍ  በሚደረገው የቁጥጥርና ክትትል ተግባር በማሳተፍ ገንቢ ሚናውን እንዲወጣ ማስቻል።

ዝርዝር ተግባራት

- የ2014 በጀት ዓመት የሕዝብ ክንፉን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለማስገባት የምክር ቤቱን የሕዝብ ክንፍ ዕቅድ መነሻ እና የኦዲት ግኝት መስሪያ ቤቶችን መነሻ በማድረግ የሕዝብ ክንፍ በአግባቡ በመለየት በውይይቶች የሚገኙበት ካልሆነም በሚዲያ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ መፍጠር፡፡

- በቋሚ ኮሚቴ ዕቅድ መሰረት ሕዝብ ክንፉን እንደመድረኩ ሁኔታ እያሳተፉ መስራት፡፡
- በየተቋማት ያሉ የሕዝብ ክንፍ አካላት በተቋማቸው ያለውን የፋይናስ ሥርዓት ግልፀኝነትና የኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢውን መረጃ በማግኘት ትግል የሚያደርጉበት ሁኔታ መኖሩ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፡፡
- በተግባር ሊያጋሙ በሚችሉ ጥንካሬና ድክመቶች ላይ መግባባት፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮችን እየገመገሙ መፍታት፡፡

ዋና ተግባር 5

- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተለውን ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የመልካም አስተዳደርና የለውጥ ሥራዎች ዕቅድ አዘጋጅተው ወደ ተግባር መግባታቸውን በክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማረጋገጥ እና ከምክር ቤቱ አባላትና ከሕዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በማጣራት ለክትትልና ቁጥጥር ሥራ መጠቀም፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

- በኮሚቴ እና በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ደረጃ የሚቀርቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር።

ዝርዝርተግባራት

- ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚቀርቡ ጥቆማዎችን ተቀብሎ እንደአግባብነቱ ለክትትልና ቁጥጥር ሥራ መጠቀም፡፡
- የኮሚቴ አባላት በተለያዩ የሕዝብ ይፋ ውይይት መድረኮች እንደአስፈላጊነቱ እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡

ዋና ተግባር 6

- ከምክር ቤቱ የተመሩ ረቂቅ ሕጎች ጥራታቸውን የጠበቁ ሆነው እንዲፀድቁ ማድረግ፤ ከዚህ በፊት የወጡ ሕጎችም ደንብና መመሪያ የተዘጋጀላቸው መሆኑን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥ፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

- ለቋሚ ኮሚቴያችን ከምክር ቤቱ በዓመቱ የሚመሩ ሕጎች ሲኖሩ የምክር ቤቱ የአሰራርና አባላት ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ጥራት ያለው ሕግ እንዲወጣ ማስቻል፡፡

ዝርዝር ተግባራት

- በረቂቅ አዋጆች ላይ በምክር ቤቱ አባላት በመጀመሪያ ንባብ ወቅት የተነሱ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን አጠናቅሮ በግብአትነት መጠቀም፡፡
- በረቂቅ አዋጆች ላይ የበሰለ ውይይት ማድረግና መመርመር፡፡
- የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አስረጂዎች ቀርበው ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
- ለሕዝብ ውይይት መቅረብ ያለባቸውን በመለየት የይፋ የሕዝብ መድረክ (public hearing) ማዘጋጀት፡፡
- በሕዝብ አስተያየት መድረክ መሳተፍ ያለባቸውን መስሪያ ቤቶችና ተቋማት መለየት፡፡
- ከሕዝብና ከሚመለከታቸው አካላት የተሰበሰቡትን አስተያየቶችና ጥያቄዎች አጠናቅሮ ማቅረብ፡፡
- ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ሪፖርትና የውሣኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ ማቅረብ፡፡
- የሚወጡ ሕጎች ምን ያህል በትክክል ጥቅም ላይ እንድሚውሉና እያመጡ ያለውንም ለውጥ መከታተል፡፡

ዋና ተግባር 7

- መስሪያ ቤቶች በድርጊት መርኃ ግብራቸው መሰረት ስለወሰዱት የማስተካከያ እርምት እርምጃ ላይ በየሩብ ዓመቱ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት ከተቋማት የሚላኩ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ ተጠያቂነት በተቋማቱ ላይ እንዲተገበር የማድረግ ሥራ መስራት፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

- የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተመደበው በጀት የአገሪቱን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ የአሰራር ሥርዓቶች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ተከትሎ በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውንና የተቀመጠላቸውን ዓላማና ግብ በማሳካት ውጤት ማስገኘታቸውን ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ችግር ያለባቸው ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃዎች በሚመለከታቸው አካላት እንዲወሰዱማድረግ፡፡

ዝርዝር ተግባራት

- ችግር ያለባቸው ተቋማት በየጊዜው ስለወስዱት እርምጃ ለዋና ኦዲተር እና ለሚመለከታቸው አካላት ስለመላከቸው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ መስራት፡፡
- ከተቋማት የመጡ የማሻሻያ ሪፖርቶች ትክክል ስለመሆናቸው በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንዲረጋገጥ ማድረግ፣
- በቁጥጥርና ክትትል ሂደት በግብረ መልሶች መሰረት ያልፈፀሙ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን ከሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎችና ከምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ጋር በመመካከር አስፈላጊው እርምት እንዲወሰድ ማድረግ፡፡
- በተደጋጋሚ የጐላ ችግር የሚታይባቸው እና መሻሻል የማያሳዩ የመንግስት ተቋማትን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዝርዝር ሪፖርትና የውሣኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ማቅረብ፡፡

<u>ግብ3.</u>

- የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አፈፃፀም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የተደረገ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ፡፡

  <u>የሚጠበቅ ውጤት</u>

  የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አፈፃፀም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ  ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

ዋና ተግባር 8

- በቋሚ ኮሚቴው፣ በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እና በኦዲት ግኝት ሪፖርት የሚቀርብባቸው መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች እየተካተቱና የተፈፀሙ መሆናቸውን ክትትል፣ቁጥጥርና ድጋፍ ማድረግ፣

የሚጠበቅ ውጤት

- ቋሚ ኮሚቴው የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎችን ትኩረት ሰጥቶ መከታተሉን ለመገምገም ማስቻል፡፡

ዝርዝር ተግባራት

- ለቋሚ ኮሚቴ ሴት አባላት ሥልጠናና የልምድ ልውውጦች እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- የሴቶች ውሳኔ ሰጭነት ሚና በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እና በኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች ተጠናክሮ እንዲቀጥልና እንዲያድግ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

- በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች ትኩረት በመስጠት ከመደበኛ ሥራ ጋራ ተካተው መተግባራቸውን መከታተል፡፡
- በሴቶች ወጣቶችና ሕፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች በተገቢ መልኩ ታቅደው መከናወናቸውን መከታተል፡፡
- የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በዕቅድ መያዙንና በተግባር ላይ መዋሉን መከታተል፡፡
- የአካል ጉዳተኞች ጉዳይንና የአርብቶ አደር ጉዳይን በተመለከተ የዕቅዱ አካል መሆናቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ፡፡
- በምክር ቤቱ በሚያዘጋጁ የሴክተር ዘለል ሥራዎችና የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ መሣተፍ፡፡
- በቋሚ ኮሚቴያችን አባላት የሚረዱ ወላጅ አጥ እና ለችግር የተጋለጡ የልጆችን ድጋፍ በወቅቱ መፈፀም፡፡

## 7. የማጠቃለያ ምዕራፍ

ይህ ምዕራፍ አጠቃላይ የኮሚቴው የዓመቱ የሥራ አፈፃፀም ማሳረጊያ፤ ከሥራ አፈፃፀሙ በመነሳት ለቀጣይ ትምህርት የሚወሰድበት፤ የዕቅድ አፈፃፀሙ ውጤቱ የሚታይበት ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ የኮሚቴው፤ የዋና ኦዲተር የሥራ አፈፃፀም እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና ተሳትፎ ምን እንደነበር ይገመገማል፡፡

ዋና ተግባር 9

- የቋሚ ኮሚቴው የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርቶች መገምገም እና ወቅታቸውን ጠብቀው ለውይይት እንዲቀርቡ ማድረግ፡፡

የሚጠበቅ ውጤት

- ወቅቱን የጠበቀ የአፈፃፀም ግምገማ ለማድረግና ዕቅድ በወቅቱ በማዘጋጀት ሥራዎችን በታቀደና ውጤታማ በሆነ መልክ መፈፀም፡፡

ዝርዝር ተግባር

- የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀትና ከአባላት ጋር በመገምገም የዳበረና የፀደቀውን ሪፖርት ለሚመለከታቸው የበላይ አካላት መላክ፡፡
- በዓመቱ የሥራ አፈፃፀም ላይ ጥልቅ ግምገማ ማድረግ፡፡

## 8.የአፈፃፀም አቅጣጫዎች

- የፌዴራል የመንግስት ተቋማት በኦዲት ግኝት ሪፖርት መሠረት  በማሻሻል በሚደረግ አገራዊ የለዉጥ ጉዞን ለማስቀጠል ያለዉ ዝግጁነት ፡፡
- የዋናዉ  ኦዲተርና ኦዲት ተድራጊ  መ/ቤቶች የዲሞክራሲ ሥራት ስር እንዲሰድ ለማድርግ  ስለመታቅዱና በተግባር ስለመፈፀሙ ክትትል ማድረግ ፡፡
- የዋና ኦዲተር መ/ቤት ተቋማዊ  ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የመዋቅር  የአደረጃጀት ለውጥ ስለማድረጉ መከታተል  ፡፡
- የዋናዉ  ኦዲተርና ኦዲት ተድራጊ  መ/ቤቶች በእቅዳቸዉ መሠረት ዉጤተማ ሥራዎች ስለመስራታቸዉ ክትትል ማድረግ ፡፡
- ኃላቀርነተንና ድህንነትን በመዋጋት በልፅግናን ለማረጋገጥ የዋናዉ  ኦዲተርና ኦዲት ተድራጊ  መ/ቤቶች በእቅዳቸዉ ስለመካተቱና በተግባር ስለመፈፅማቸው መከታተል ፡፡
- ማንኛውም ዕቅድና ቼክሊስት በሚመለከተው ኮሚቴ አባላት ተዘጋጅቶ ለአባላት ቀርቦ አስተያየትና ተጨማሪ ግብኣት ተሰጥቶበት ወደ ሥራ ይገባል፡፡
- ሁሉም ሥራዎች ማለትም ዕቅድ፣ ስምሪት፣ ሪፖርት፣ ግምገማና ሌሎች የአባላትን ተሳትፎ መሰረት ባደረገ መልኩ ይከናወናሉ፡፡
- ማንኛውም ሥልጠና እና ስምሪት የሥራ አግባብን መሰረት አድርጎ ይፈፀማል፡፡
- ዕቅድ በየወቅቱ እንደአስፈላጊነቱ ይከለሳል፤ይታረማል፡፡
- ዕቅድና ሪፖርትን በዝርዝር በመገምገም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- በክትትልና ቁጥጥር የተገኘ ውጤትን መገምገምና ከዚሁ የሚገኘውን ትምህርት ይወሰዳል፡፡
- ከዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ጋር ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ይደረጋል፡፡
- ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በሚያገናኙን ተግባራት በቅንጅት የጋራ ቼክሊስት በማዘጋጀት የመተግበር አቅጣጫ መከተል፡፡
- ዘርፈብዙ ተግባራትን ከዕቅድ እስከ ክንውን በመከታተል እጥረት ሲኖር የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፡፡
- የኮሚቴውን ቅንጅታዊ አሰራር የሚያጠናክሩ ተግባራትን አዘውትሮ መጠቀም፡፡
- የቢሮና የመስክ ሥራዎችን ቆጥሮ ቼክሊስት በማዘጋጀት መከታተል፡፡

- በጀትን ቆጣቢ በሆነ መንገድ መጠቀም፡፡
- ሥራን መፈፀም ብቻ ሳይሆን በጥራት፣ተነሳሽነት እና ተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን፡፡
- የቡድን ሥራ መንፈስን ማዳበር፤ መደበኛ የቋሚ ኮሚቴ መድረኮችን አጠናክሮ መፈፀም፡፡
- ከምክር ቤቱ እና ከመንግስት ተጠሪ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ለቀጣይ ሥራ መጠቀም፡፡
- ከመድረኮች በኋላ የውሎ ግምገማ በማድረግ ስህተቶችን በወቅቱ እያረሙ መሄድ፡፡
- ከኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት ጋር በመደበኛ ሥራና በመስክ ቅንጅታዊ ሥራ በቀጣይ ተጠናክሮ ተግባራት ይፈፀማል፤ ከመስክ ምልከታ በኋላ በተገኙ ግኝቶች ላይ ከሚመለከታቸው ተቋማት ኃላፊዎች ጋር በአካል ውይይት ማድረግ፤ በኦዲት ግኝቱ መሰረት በሚገኙት ክፍተቶች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድለ ሚመለከተው (feed back) ይሰጣል፡፡
- የሚደርሱ ጥቆማዎችንና ቅሬታዎችን መሰረት አድርጎ ከፌደራል ዋና ኦዲተርና ከምክር ቤቱ ጋር ተገናኝቶ የቀረበውን ቅሬታና ጥቆማ መፍታት፡፡

## 9. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት

- የኮሚቴው አባላት በሳምንት ሦስት ቀንናት፤ ሰኞ፣ ረቡእና አርብ ውይይትና ግምገማ ያደርጋሉ፤ አጠቃላይ የዕቅድ ግምገማ በየወሩ በማድረግ ለምክር ቤት አፈጉባዔና መንግስት ተጠሪ ሪፖርት ይቀርባል፡፡
- በተያዘው ዕቅድ መሰረት የመስክ ምልከታ ይደረጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድንገተኛ መስክ ምልከታ በማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡
- ሁሉም ውይይቶች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በሰነድነት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
- ተቋማት የሚሰጧቸውን ግብረመልሶች መጠቀማቸውን ክትትል ያደርጋል፡፡
- በክትትልና ቁጥጥር ቼክሊስት መሰረት ሥራዎችን የመከታተልና መቆጣጠር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡
- የኮሚቴው አመራር ለአባላት የተሰጣቸው ሥራ በቼክሊስቱ መሰረት የትኛውን ሥራ መቼና እንዴት መፈፀም እንዳለባቸው ክትትል ይደረጋል፡፡
- የዋና ኦዲተር የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት የሩብ ዓመቱ እስከ 30ኛው ቀን እንዲሁም የኦዲት ግኝቶች እንደተጠናቀቁ እንዲላኩ ይደረጋል፡፡

- የመደበኛ ሪፖርት በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ ሩብ ዓመቱ ካለፈ እስከ 5ኛው ቀን ድርስ ሪፖርት ይቀርባል፡፡
- በመስክ ምልከታ ላይ የተመደቡ የኮሚቴ አባላት ከመስክ መልስ እስከ 5ኛው ቀን ድረስ የጽሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡
- በተለያዩ ሥልጠናዎች የተካፈሉ አባላት በሥልጠና የተገኘውን ልምድ በተመለሱ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለቀሩት አባላት እንዲያካፍሉ ይደረጋል፡፡
- ወርኃዊ ሪፖርት በወቅቱ የማጠናቀቅና ለበላይ አካል የማቅረብ ሥራ ይሰራል፡፡

## 10. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ ሐሳቦች

### 10.1 ችግሮች

- በመስክ ምልከታም ሆነ በሕዝብ ይፋ መድረክ የመስሪያ ቤት ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ላይገኙ ይችላሉ፡፡
- የመስክ ምልከታ አስፈላጊው ግብአት ተሟልቶ በተያዘለት ጊዜ ላይካሄድ ይችላል፤ እንዲሁም የኮሚቴው የሥራ ቀናት በመንግስት ተጠሪ እና በሌሎች ተደራራቢ ሥራዎች ሊያዝ ይችላል፡፡
- ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች በሚፈለገው መልኩ የኦዲት ሪፖርቶችን እንደአጋዥ አድርገው ላይወስዱ ይችላሉ፡፡
- ቋሚ ኮሚቴው የሚያደርጋቸውን የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት በተገቢው እና ወቅታዊ በሆነ መልኩ ለሕዝብ ከማድረስ አንፃር የሚዲያ ሽፋን ላያገኙ እና ተደራሽ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

### 10.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

- ዋና ኦዲተር ዓመታዊ ዕቅዱንም ሆነ የየሩብ ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ የሚልክበትን መርኃግብር ማስቀመጥ፡፡
- የመስክ ፕሮግራሙን አስቀድሞ ለምክር ቤት በማሳወቅ ክትትል ማድረግ እና ለኮሚቴው በተያዙ ቀናት ሥራዎችን አጣጥሞ መስራት፡፡
- የመስሪያ ቤት ኃላፊዎች በመስክ ምልከታም ሆነ በሕዝብ ይፋ መድረክ ላይ ትኩረት ሰጥተው አስቀድሞ ማሳወቅ፡፡

- ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የኦዲት ውጤትን እንደ አንድ አጋዥ የመከታተያ መሣሪያቸው አድርገው እንዲወስዱት ግንዛቤው እንዲፈጠር በጎንዮሽ ግንኙነትና በአመራሩ በኩል መፈፀም፡፡
- ለሚዲያ አካላት ዕቅዳችንን በምክር ቤቱ ጽ/ቤት በኩል የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ማድረግ፡፡

## 11.ማጠቃለያ

የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅዱን ሲያዘጋጅ ባለፈው ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም የነበሩ ጥንካሬዎችን፣ ውስንነቶችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችን እና መልካም አጋጣሚዎችን በመገምገም፤ ክፍተቶችን በመሙላት ተጠባቂ ሚናውን በተሻለ ብቃትና ውጤታማነት መከወን የሚያስችለውን አቅጣጫ በማስቀመጥ ነው፡፡ የዋና ኦዲተር ግኝት የክትትል የቁጥጥርና የድጋፍ ሥራ መስጠት ሥራን ቁልፍ ተግባር ማድረግ እና ሦስት ዓበይት ግቦች በማስቀመጥ ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች ላይ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ሥራዎች የትኩረት አቅጣጫዎች በማስቀመጥ የ2014 ዓ.ም. ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 26 አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችን የሕዝብ ይፋዊ መድረክ /ሄሪንግ/ የምናካሂድ ሲሆን 6 የገጠርና 6 የከተማ በድምሩ 12 የመስክ የሥራ ጉብኝት የሚደረግ ይሆናል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የወጠናቸውን ዕቅዶች በስኬት ለመፈፀም የኮሚቴው አመራሮችና አባላት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ሁለንተናዊ አቅሞቻቸውን አቀናጅተው ለጋራ ውጤታማነት ሊረባረቡ ይገባል፡፡

**የጊዜ ሠሌዳ**

| | የሚከናወኑ ተግባራት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዕቅድ ማቀድ፣ | ✓ | | |
| 2 | ከቋሚ ኮሚቴ አባላት ጋር የጋራ ማድረግ፣ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 3 | የባለድርሻ አካላት ዕቅድ ማቀድ | ✓ | ✓ | |
| 4 | ከባለድርሻ አካላት ጋር እቅዱን የጋራ ማድረግ፣ | ✓ | | |
| 5 | የመስክ ምልከታ ማካሂድ፣ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 6 | ይፋ የሕዝብ መረክ ማካሄድ፣ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 7 | የስድስት ወር ግምገማ ማካሄድ፣ | ✓ | | ✓ |
| 8 | ዓመታዊ ግምገማ ማድረግ የዓመታዊ ሪፖርት፣ | | | ✓ |
| 9 | ከምክር ቤቱ የተመሩ ረቂቅ ሕጐች ጥራታቸውን የጠበቁ ሆነው እንዲፀድቁ ማድረግ | | | |